**ሳምንታዊ ዜና (ሚያዝያ 5 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**የመከላከያ ከባድ መኪናዎች ከያሉበት ወደቀድሞው አየር ማረፊያ ግቢ እንዲሰባሰቡ ታዘዙ፣ በሳሞራ የኑስ ሰብሳቢነት ከፍተኛ የጦር አለቆች ስብሰባ ተቀመጡ፣ በሰሜን ጎንደርና በምሥራቅ ኦጋዴን ችግር አለ፣ በመብራት ሃይል ሰበብ በርካታ የፋብሪካ ሠራተኞች ሊባረሩ ነው ተባለ፣ በሳምንት 2 ቀን ከጠዋቱ 12 እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት መብራት ይጠፋል፣ የመከላከያ ዘመቻ መመሪያ ከሌተናል ጄኔራል አበባው ተነጥቆ ለሕወሓቱ ጄኔራል ተሰጠ፣ ሜ/ጄ/ል ስዩም ያስጨረሰው ጦር በመዳከሙ ወደሁዋላ ወረዳ ተመለሰ** »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ያንብቡ ...................**

የወያኔና የሻዕቢያ ፍጥጫ ከቀን ወደ ቀን እያየለ መምጣቱንና ሁኔታው አደገኛ አዝማሚያ መያዙን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀኃፊ ባንኪሙን ገለፁ::

ሁለቱ ቡድኖች ከጫካ ጀምሮ ሲሻኮቱ የመጡ እና አሁንም እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እየተባባሉ በሀገርና በሕዝብ ሐብት እየቀለዱ የሚገኙት እነዚህ ቡድኖች ሰሞኑን ከመቸውም በበለጠ ሁኔታ ጦራቸው ተፋጥጦ እንደሚገኝ ተመድ ገልጿል::

ሻዕቢያ የድንበር አካላዩ ኮሚሽን የወሰነልኝን በመሬት ላይ ተግባራዊ ይሁንልኝ ከዚያም ውይይት ማድረግ ይቻላል እያለ በሚወተውትበት በአሁን ወቅት ፈፅሞ የሕዝብ ድጋፍ የሌለው ወያኔ ደግሞ በአሰብ ጉዳይና በመሰል ሁኔታው ላይ ቅድሚያ መወያየት አለብኝ እያለ የኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት ከንቱ ሙከን እያደረገ እንደሚገኝ ሁኔታውን የሚከታተሉ የወታደራዊ ባለሙያዎች ይገልፃሉ ::

ያለህዝብ ይሁንታ ወያኔ ወዶ እና አጨብጭቦ አሰብን ጭምር ያስረከበ ሲሆን ዛሬ ከጦሩም ጥያቄ ሲበዛበትና ፍፁም የሕዝብ ድጋፍ እንደሌለው ሲያረጋግጥ በአሰብ ጉዳይ ላይ የሕዝብ ድጋፍ አገኛለሁ በሚል ሰንካላ ምክንያት እየተሯሯጠ መገኘቱ አሳዛኝና በሕዝብና በሐገር ላይ የሰራውን አስነዋሪ ተግባር እንደመድገም ይቆጠራል ሲሉ እነዚሁ ወታደራዊ ባለሙያዎች ይገልፃሉ::

በአሁኑ ሰዓት የወያኔና የሻዕቢያ ጦር ተፋጥጦ ባለበት ወቅት እነ መለስ የአማራና የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ከፍተኛ የጦር ጄኔራሎችን ከስልጣናቸው እያነሱ የቁም እስረኛ ማድረጋቸውን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

ወያኔ በሠራዊቱ አዛዦች ላይ እምነት እያጣ በመምጣቱ በርካታ መኮንኖችን በየምክንያቱ ለእስር እየዳረገ እንደሚገኝ የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገ□ፀው በተለይም በሱማልያ በአለቆቹ ትዕዛዝና አይዞህ ባይነት ዘምቶ ፍዳውን ማየት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶና በኦጋዴንም ከኦብነግ ጋር በሚያደርጋቸው ውጊያዎችበየጊዜው በሚደርስበት ከፍተኛ ኪሣራ የተነሳ በገዛ ሹሞቹ ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ እያሳደረ በመምጣቱ በሰበብ አስባቡ አፍሶ ለእስር እየዳረጋቸው መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል::

በሠራዊቱ ውስጥ ለብዙ ዓመታት ሲሰሩ የነበሩ እና ለቀድሞው ስርዓት ሲያገለግሉ የነበሩ ነገር ግን ወያኔ ይጠቅሙኛል ብሎ ወደስራቸው የመለሳቸውና በረሀ ለብዙ ዓመት በትግል ላይ የነበሩ የአማራና የኦሮሞ ተወላጅ መኮንኖችን ጨምሮ በርካቶችን በቀብሪደሀርና በጅጅጋ እንዲሁም በታጠቅ የጦር ካምፖች አስሯቸው እንደሚገኝ ምንጮቹ ገልፀዋል::

ወያኔ በአግባቡ ጦሩን አልመራችሁም፣ ለጠላት መረጃ አሳልፋችሁ እየሰጣችሁ ነው በሚል ሰንካላ ምክንያት እያፈሰ ለእስር እየዳረጋቸው ሲሆን፣ በኦጋዴን ውስጥም ያለውን ጦር የሚሰሩትን ከወታደር እስከ ሌተና ኮሎኔል ማዕረግ ድረስ ያሉትን የአማራና የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ቀብሪደሀር ለተወሰኑ ቀናት በካምፑ ውስጥ ካጐራቸው በኋላ ወደ ጅጅጋ ወታደራዊ ካምፕ እንደሚወስዳቸው ምንጮቹ ገልፀው በአሁን ሰዓት ከ200 በላይ ከተራ ወታደር እና ሌተናል ኮሎኔል ማዕረግ ያላቸው የሠራዊቱ አባሎች ታስረው እንደሚገኙም አስረድተዋል::

ወያኔ የስልጣን እድሜዬን ያራዝመልኛል ብሎ ከተበተነው ከደርግ ሠራዊት ውስጥ በሙያቸው መልምሎ የቀጠራቸው እና በረሀ አብረው በትግል ላይ የነበሩትን ጨምሮ ሰበብ እየፈለገ ለእስር ከመዳረጉም በላይ ቤተሰቦቻቸው በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉና የት እንደደረሱ እንኳዋን እንዳያውቁ በምስጢር በጅጅጋና በቀብሪደሀር ወታደራዊ ካምፖች እያሰራቸው መሆኑንና በዚህም የተነሳ በሰራዊቱ ውስጥ ከፍተኛ የሞራል ውድቀት እንደደረሰ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀው በተለይ ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ የተቃዋሚ ኃይሎች አባልና ደጋፊ ናችሁ በማለት በሺዎች የሚቆጠሩ የሠራዊቱ አባሎች ያለምንም ክፍያ የተባረሩ መሆኑን አውስተው የአየር ኃይሉ ዋና አዛዥ ሜ/ጄ/ል አለምሸት ደግፌም የዚሁ ሰለባ እንደሆነ ምንጮቹ አብራርተዋል::

አሁንም ከ40 በላይ መኮንኖች በቀብሪደሀርና በጅጂጋ ታስረው የሚገኙ ሲሆን በተለይ እራሱን የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጭ ነኝ ብሎ ከሚጠራው ታጣቂ ኃይል ጋር ውጊያ ከተጀመረ ጀምሮ በርካታ መኮንኖች ላይ ጥርጣሬውን እያጐላ የመጣው ወያኔ ለእስር እየዳረጋቸው ሲሆን ሂደቱ አሁንም እንደቀጠለም አብራርተዋል::

በተያያዘ ዜና በርካታ ከፍተኛ መኮንኖች ሰበብ እየተፈለገባቸው ከመታሰራቸውም በተጨማሪ የቁም እስረኛ እንደሆኑና በየቢሮው የሰዓት ፊርማ እየፈረሙ እንዲወጡ እንደሚደረግ የመከላከያ ምንጮች አጋለጡ::

ከበረሀ ጀምሮ ውሃ በጀሪካን እያመላለሰ ሲላላካቸው የነበረውና በኋላም የምስራቅ እዝ ዋና አዛዥ ሆኖ ወያኔን ሲያገለግል የነበረው ሜ/ጄ/ል ባጫ ደበሌ የቁም እስረኛ እንደሆነ ምንጮች ገልፀዋል::

ሜ/ጄ/ል ባጫ ደበሌ በወያኔ ወታደራዊ ተቋም ውስጥ የብሔር ስብጥር አለ ለማሰኘት ተብሎ የጄኔራልነት ማዕረግ ከተሰጣቸው መካከል አንዱ ሲሆን፣ በ1999 ዓ.ም የምስራቅ ዕዝ 2 ክፍሎችን ወደ ሱማልያ እንዲዘምቱ ተደርጐ መጀመሪያ ሞቃዲሾ ለመግባት በነበረው ውጊያ ቁጥራቸው የበዛ የወያኔ ወታደሮች በመሞታቸው የተነሳ ለጊዜው ከእዙ ተነስቶ ወደመከላከያ ዋና መስሪያ ቤት ውስጥ እንዲዛወር ተደርጐ የነበረ ቢሆንም በአሁን ወቅት የቁም እስረኛ መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል::

በወቅቱ ጦሩን ለመምራት እንኳዋን እድል ሳይሰጠው የምስራቅ እዝ ምክትል አዛዥ ብርጋዴየር ጄኔራል ስዩም ሐጐስ የተባለው የሕወሓቱ ጄኔራል እንደነበረና ሞቃዲሾ ድረስ ዘልቆ ጦሩን ሲያስጨርስ እንደበረ ያስታወሱት ምንጮች የአይንህ ቀለም አላማረንም ካልሆነ በስተቀር ባጫ ደበሌ ማዘዣው ጅጅጋ እንደነበረና በአግባቡ ጦሩን ለመምራት እድል እንዳልነበረው እየታወቀ ጦሩን አስጨርሰሀል ተብሎ ለጊዜው ከምስራቅ ዕዝ አዛዥነት ተነስቶ በመከላከያ ትምህርትና ስልጠና የአንድ መምሪያ አዣዥ ሆኖ ሲሰራ ቢቆይም በአሁን ወቅት ግን የቁም እስረኛ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን፣ ሌሎቹ ለጊዜው ስማቸው ያልታወቁ 3 ጄኔራሎች በተመሳሳይ ሁኔታ የቁም እስረኛ እንደሆኑ ምንጮቹ ገልፀው አንደኛው ሌተናል ጄኔራል አበባው ታደሰ የአማራ ብሔር ተወላጅ ሳይሆን አይቀርም ሲሉም ያላቸውን ግምት ይገልፃሉ::

ወያኔ የራሴ ናቸው የሚላቸውን ካድሬዎቹን በተለይም የአማራና የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ላይ ከቀን ወደ ቀን ከፍተኛ ጥርጣሬ ውስጥ እየከተታቸው ያለአንዳች ጥፋት ለእስር እየዳረገና የቁም እስረኛ ከማድረጉም በተጨማሪ በቅርቡ ደግሞ የማዕረግ ገፈፋ ሊያደርግ እንደሚችል ምንጮቹ ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል::

ምንጮቹ በተለይ በሜጀር ጄኔራል ባጫ ደበሌ ላይ ይህ እርምጃ ተወሰደበት የተባለው ጦሩን አስጨርሰሃል በሚል ሰበብ ቢሆንም ዋናውና ትልቁ ወያኔ አይን ውስጥ ሊገባ የቻለው በአንድ ወቅት ሁለት የኦሮሞ ተወላጅ ጄኔራሎችን ጨምሮ በርካታ ወታደሮች ከመክዳት ጋር ተያይዞ «የቅርብ ጓደኞችህ ናቸው ታውቃለህ አንተም ቦታና ጊዜ እስከሚመቻችልህ ድረስ ነው»በሚል ለቁም እስረኛነት እንደተዳረገ የጠነከረ ግምታቸውን ሰጥተው በሱማልያ ጦሩን ሲያስጨርስ የነበረው የሕወሓቱ

ብርጋዴየር ጄኔራል ስዩም ሐጐስ የሜጀር ጄኔራልነት ማዕረግ ተሰጥቶት የምዕራብ እዝ ዋና አዛዥ ሆኖ እንደተሾመም ምንጮቹ በዝርዝር አስረድተዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔው ቡድን ለብዙ ዓመታት በትግል ላይ ነን እያለ ለፖለቲካ ፍጆታ ያህል ያውራ ከእንጂ እውነታው ከዚህ የተለየ መሆኑን በተለያዩ አጋጣሚዎች እያሳየ ሲሆን በቅርቡም የታየው ይኸው መሆኑን የመከላከያ ምንጮች ገልፀዋል።

በተለይም የዘመቻ መምሪያ ኃላፊ የነበረው ሌተና ጄኔራል አበባው ታደሰ ተነስቶ የሕወሓቱ ሜጀር ጃኔራል ገብረ እግዚአብሔር መብርሐቶ በቦታው የተተካ ሲሆን፣ ገብረ እግዚአብሔር የተባለው የሕወሓቱ ጀኔራል ቀድሞ በደህንነት መመሪያ የኦፕሬሽን ክፍል ኃላፊ ሆኖ መምሪያ ኃላፊ የነበረ ሲሆን ወያኔ የራሴ ናቸው የሚላቸውን የሕወሓት ጄኔራሎችን ብቻ በሌሎች ብሔር መኮንኖች በራሳቸው እየተኩ ሲሆን፣ ይህ እንቅስቃሴ እስከ ዝቅተኛው የጦር ክፍል ድረስ እንደሆነም ምንጮቹ አብራርተዋል።

በቅርቡ የቁም እስረኛ ከሆኑት አራት ጄኔራሎች መካከል ሌተና ጀኔራል አበባው ታደሰ አንዱ ሲሆን፣ ከመከላከያ ዘመቻ መምሪያ ኃላፊነቱ ተነስቶ በሜ/ጀ/ል ገ/እግዚአብሔር መብርሀቶ ተተክቶ ለስሙ ቢሮ እየገባና ፊርሞ እንዲወጣ ብቻ ተደርጐ ያለ ሲሆን በአሁን ሰዓት በመከላከያ ውስጥ ያለው መዋቅር

ሜ/ጄ/ል ዮሐንስ ገ/መስቀል የደህንነት መምሪያ ኃላፊ ትግሬ

ሜ/ጀ/ል ገ/እግዚአብሔር መብርሐቶ የዘመቻ መምሪያ ኃላፊ ትግሬ

ሜ/ጄ/ል ታደሰ ወረደ የትምህርትና ስልጠና መምሪያ ኃላፊ ትግሬ

ሜ/ጄ/ል ሞላ ኃ/ማርያም የአየር ኃይል ጥብቅ አዛዥ ትግሬ፡

የሰሜን እዝ አዛዥ ሜ/ጄ/ል ሳእረ መኮንን (ትግሬ)

የምዕራብ እዝ አዛዥ ሜ/ጄ/ል ስዩም ሀጐስ (ትግሬ)

የምስራቅ እዝ አዛዥ ሜ/ጀ/ል አብርሐም ገ/እግዚአብሔር (ትግሬ)

የማዕከላዊ እዝ አዛዥ ሜ/ጀ/ል ዮሐንስ ገብረ መስቀል ከደህንነት መምሪያ ኃላፊነቱ በተጨማሪ በበላይነት የሚቆጣጠረው የጦር ክፍል ሲሆን ሰውየውም ትግሬ መሆኑን የመከላከያ ምንጮች አስረድተው የጦር ኃይሎች አዛዥና ኢታማዦር ሹም መለስ ዜናዊና ሳሞራ የኑስ መሆናቸውን በዝርዝር አስረድተዋል። በአንድ ብሔር የበላይነት ተጀምሮ የተጠናቀቀው የመከላከያ መስሪያ ቤት የተባለው ተቋም ጥቂት የብሔር ተዋፅኦ ያሳያሉ ተብለው ተሹመው የነበሩት ጄኔራሎችም ለቁም እስረኝነት መዳረጋቸው በጣም የሚያሳፍር መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።

በተለይም ብሔሮቻቸውን ያስደቡ ለሆዳቸው እንጂ ለሀገርና ለወገን ክብር የሌላቸው የወያኔ ቡችሎች የሆኑት እነዚሁ ጄኔራሎች ተብዬዎች በትምህርትም ሆነ በእውቀት ከሕወሓቶች በላይ መሆናቸውን እያወቁ እንደኩዋስ ሲጫወቱባቸው ዝም

ማለታቸው በእጅጉ አሳፋሪና አሳዛኝ ፍጡር መሆናቸውን ያረጋገጡበት ወቅት ነው ሲሉ እልህና ቁጭት በተቀላቀለበት ስሜት ምንጮች ገልፀዋል።

በቅርቡም 44ኛ ዳሎል ክፍለ ጦር የተመሰረተበት 8ኛ ዓመት እና በሞቃዲሾ እና በባይደዋ ያለቀበትን ምክንያት በማድረግ ሰኞ መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም በጅማ ከተማ ማክበሩን የወያኔ የጦር ክፍል ገልጿል።

የምዕራብ እዝ አዛዥ ሜ/ጄ/ል ሰዩም ሐጐስ ይህንኑ የጦር ክፍል እየመራ አስጨርሶ መልሶም «ጀግና» እያለ እያወደሰና እያሾፈበት የላቀ ጀብድ ለፈፀሙ የጦር ክፍሉ አባላት ስልጣን ሰጠ ይባል እንጂ በወቅቱ በአብዛኛው ነባር የሠራዊቱ አባላት በውጊያው ያለቁ በመሆኑ ለማስመሰል የተሰራ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል።

በኦጋዴንና በሞቃዲሾ በተከታታይ በተደረገ ውጊያ ከፍተኛ ኪሣራ ከደረሰባቸው 20ኛ ክ/ጦር፣ 13ኛ ክፍለ ጦር በተጨማሪ ይህ 44ኛ ዳሎል ክፍለ ጦር የተባለው ሲሆን፣ ዛሬ የጦሩን ሞራል ለመገንባት በሚል እሳቤ ብቻ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲሉ የምስክር ወረቀት እየሰጡ እየሸነገሉ እንደሚገኝ ምንጮቹ ገልፀው ለሟች ወታደር ቤተሰቦች መርዶ እንኳዋን ከጥቂቶቹ በስተቀር እንደልተነገራቸው ጨምረው አስረድተዋል።

ሰዩም ሐጐስ እራሱ ጦሩን አስጨርሶና በርካቶቹን ሲያስረሽን ቆይቶ ዛሬ መልሶ ሸላሚ ሆኖ መምጣቱ አላዋቂነቱንና ጨካኝነቱን ያሳያል ሲሉም ምንጮች ገልፀዋል።

ወያኔ ሰሞኑን ከወትሮው በተለየ መልኩ በቀድሞው የምድር ጦር መመሪያ ወይም የቀድሞው አየር ማረፊያ ግቢ ውስጥ የመከላከያ ታርጋ የለጠፉ የጭነት መጫኛ ቮልቮ መኪኖችን ከያሉበት ተሰብስበው እንዲገቡ ማድረጉን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ።

በዚህም መሠረት ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ለግዳጅ ተበታትነው የነበሩት እነዚሁ ከባድ መኪኖች ከሰኞ መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም ቀን ጀምሮ ወደ ቀድሞ አውሮፕላን ማረፊያ እየገቡ ሲሆን እስከ ረቡዕ ሚያዝያ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ 250 ከነተሳቢዎቻቸው ገብተው እንደነበርም ምንጮቹ ገልፀዋል።

በአሁን ወቅት ከሻዕቢያ ጋር ከፍተኛ ፍጥጫ ላይ ያለው ወያኔ ከዚህ ቀደም እንዲህ ያለ ትዕዛዝ አስተላልፎ የማይታወቅ ሲሆን አሁን በአንድ ላይ በሐገሪቱ ውስጥ በወታደራዊ ግዳጅ ላይ ተሰማርተው የነበሩት እነዚሁ መኪኖች ለምን እንደተፈለጉ በትክክል ለመግለፅ ምንጮቹ ቢቸገሩም ዞሮ ዞሮ ለወታደራዊ ግዳጅ ለማሰማራት እንደሆነም ገልፀዋል።

ሌሎች ውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደገለፁት ከሆነ ደግሞ በአሁን ሰዓት ወያኔ የገንዘብ እጥረት ስላለበት ጦሩን ከቦታ ወደ ቦታ ለማዛወር በሕዝብ ማመላለሻ

አውቶቡስ ኪራይ ከፍተኛ ወጪ ስለሚያስወጣው ይህንኑ ለማስቀረት ተብሎ የታቀደ መሆኑን ጠቁመው ብዙ የጦር አባላትንም ሆነ መሣሪያ ለመጫን የሚችሉ መኮንኖች መሆናቸውንም በዝርዝር ገልፀዋል::

የጦር አዛዥ መኮንኖች በአስቸኳዋይ ይሰብሰቡ ብሎ የጦር ኃይሎች ምክትል አዛዥ ጄኔራል ሳሞራ የኑስ ትዕዛዝ ማክሰኞ መጋቢት 30 ቀን 2000 ዓ.ም ከጧቱ 3 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት ድረስ በመኮንኖች ክበብ አዳራሽ ስብሰባ ሲያካሂዱ እንደነበርም ምንጮች ገለፁ::

የጦር ጄኔራሎችን ሰብስቦ በወቅታዊ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ላይ ውይይት ሲያደርግ እንደነበረ የገለፁት ምንጮች በተለይም በምስራቅ ኦጋዴን፣ በሰሜን ጐንደር፣ በሰሜን ምስራቅ አፋር በደፈጣና በፊት ለፊት ውጊያ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑን አምነው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ምን አይነት እርምጃ ብንወስድ ልናጠናቅቅ እንችላለን በሚለው ላይ በዝርዝር የተወያዩ ቢሆንም ሁሉም የየበኩሉን ሀሳብ ከመሰንዘር ባለፈ የረባ ውሣኔ ላይ ሳይደርሱ እንደተበተኑም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ያለምንም እውቀት በሀገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን የሙሉ ጄኔራልነት ማዕረግ ተሸክሞ ያለው ሳሞራ የኑስ ካርታ አንብቦ የውጊያ ትዕዛዝ መስጠት የማይችል በአልኮልና በሲጋራ ሱስ የተጠመደ ለመለስ ዜናዊ ቅርብ የሆነ ሰው መሆኑን የገለፁት ምንጮች ሁልጊዜ ስብሰባ ሲመራ ሲል ጄኔራል መኮንኖቹ እየተያዩ እንደሚስቁበት ሁሉ የዚያንም ቀን በተመሳሳይ ሲሳሳቁበት እንደነበረም ምንጮቹ የታዘቡትን ገልፀዋል::

በኦጋዴን በኩል ተደጋጋሚ ግጭት እያደረገ በርካታ የወያኔ ወታደሮች እየቆሰሉ ወደ ጅጅጋ ሆስፒታል እየገቡ ሲሆን፣ እዚያም አስተማማኝ አይደለም በማለት ሰሞኑን ደግሞ ሐረር ከተማ ቀላድ አምባ ተብሎ በሚጠራው ሆስፒታል ውስጥ እያስገባቸው መሆኑንም ምንጮቹ የሆስፒታል ሠራተኞችን ዋቢ አድርገው ገልፀዋል::

በሰሜን ጐንደር በኩልም በተመሳሳይ ሁኔታ ድንገተኛ ጥቃት ተቃዋሚ ታጣቂ ኃይሎች እየሰነዘሩ ከባድ ጉዳት እየደረሰባቸው ሲሆን፣ ቁስለኞች ወደ ደባርቅ እየተጓጓዙ እንደነበርና ሰሞኑን ግን ወደ ባህርዳር እንዲጓጓዙ መደረጉንም እነዚሁ የመከላከያ ምንጮች ገልፀዋል::

በሌላ በኩል የመብራት ኃይል ኮርፖሬሽን የተባለው የወያኔ ባለሥልጣናት የተሰገሰጉበት መስሪያ ቤት ከየካቲት ወር አጋማሽ ጀምሮ ለግማሽ ቀን በፈረቃ መብራት እንዲጠፋ ሲያደርጉ ቆይተው የቴክኒክ ብልሽት ነው እያሉ ሕዝቡን ሲዋሹ የሰነበቱ ቢሆንም እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንዲሉ የወያኔ ዋሾ ባለሥልጣናት

ባለፈው ሳምንት የተፈጠረውን ችግር አምነው ችግሩም ቀጣይ መሆኑን በይፋ ገልፀዋል፡፡

ከአንድ ወር ከ20 ቀን በላይ ሕዝቡን ደብቀው ፈረቃ እንዲጠቀም ያደረጉትን በቴክኒክ ብልሽት ነው እያሉ ሲዋሹ ቢቆዩም ወቅቱ ደርሶ እራሳቸው መልሰው ከአቅም ማነስ የተፈጠረ ነው በማለት በይፋ በወያኔው ምህረት ደበበ በሚባለው ስራ አስኪያጅ አማካኝነት የገለፁ ሲሆን፣ ችግሩ እስከ 3 ወር ድረስ ሊዘልቅ እንደሚችልም አምነዋል፡፡

በተለይም በአሁን ወቅት በአምስት ዋና ዋና ቦታዎች ማለትም ጄኔረተሮች ተተክለው አጋዥ ኃይል እንዲሰጡ ተደርገዋል ለነዚህም ለእያንዳንዱ በወር 100 ሚሊዮን ብር እያወጣን ነው በማለት የገለፁ ቢሆንም የመብራት ኃይል ምንጮች እንደገለፁት ከሆነ ግን ያለውን የመብራት አቅም ሙሉ በሙሉ በአግባቡ ብንጠቀምበት ይበቃ ነበር፡፡ ነገር ግን አሁንም ዋሽተው ዝም ይላሉ እንጂ ለሱዳን የተሰጠው ኃይልስ ለምን ለሕዝቡ አልተገለፀም? ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡

ገና መስመር ዝርጋታ የተጀመረ አስመስለው እያወሩ ያሉት ባለሥልጣናቱ ዛሬ ሱዳን ከፍተኛ የመብራት ኃይል እያገኘች ያለችው ከማን እንደሆነ እየታወቀ ይህንንም በግልፅ ለሕዝቡ አለመንገራቸው አሁንም በሕዝቡ ላይ የሚሰሩት ሸፍጥ እንዳለ ነው ሲሉም በምሬት ይገልፃሉ፡፡

ሌላው በአዲስ አበባና በአካባቢዋ እጅግ ከፍተኛ ፋብሪካዎች ያሉበት መሆኑ እየታወቀ ፋብሪካዎቹ ያለምንም ስራ እንዲቆሙ መደረጉ ሠራተኞችን ከስራ እንዲፈናቀሉ፣ ባለሀብቱም እንዲዳከም ሆን ተብሎ የተወሰደ እርምጃ መሆኑን የገለፁት አንድ የፋብሪካ ባለቤት በዚህ አይነት መልክ 15 ቀን መቀጠል አይቻልም በጄኔሬተር ይሁን ቢባል ዛሬ አንድ ሊትር ነዳጅ 7 ብር ከ70 ሳንቲም ገብቷል ታዲያ እንዴት ያዋጣናል ሲሉም ይጠይቃሉ፡፡

አክለውም ዋናው የሚያዋጣን ሠራተኛን መቀነስ ብቻ ነው ስለዚህ ከ15 ቀን በኋላ ደግሞ ሁሉም ፋብሪካዎች ይህንኑ ተግባራዊ ያደርጋሉ ሲሉ በወያኔ መሠሪ ስራ በቁጭትና በእልህ ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

በአዲስ አበባ ሻይ ቡና ቸርችረው እናድራለን ብለው በመቶ ሺህ የሚቆጠር ገንዘባቸውን አፍስሰው እየሰሩ ያሉት ባላካፌዎችም እጅግ ከመማረራቸውም በላይ ግብር እና ኪራይ ለመክፈል ቀርቶ ለሰራተኞች ደመወዝ እንኳዋን ለመስጠት እንቸገራለን ሲሉም እያማረሩ ይገኛሉ፡፡

እንደወያኔ የመብራት ኃይል ባለሥልጣናት ገለፃ ከሆነ በሳምንት ሁለት ቀን ከጧቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ በፈረቃ መብራት የሚጠፋ መሆኑን

የገለፁ ቢሆንም በዚህም መሀከል ከፈረቃ ውጭ እንደሚጠፉ ከገለፃቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡